# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከፌብርዋሪ 1-28/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም ከማርች 1-31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ


ማርች 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1. እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈው የፌብርዋሪ ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ እና ሶስተኛዉ አስር ቀናት ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፣ በአንጻሩ በሁለተኛዉ አስር  ቀናቶች ላይ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የደመና መጨመር ከመታየቱም በላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በቁሉምሳ 24.5፣ በወራቤ 8.8፣ በጅማ 7.9፣ በኢጃጂ 7.8፣ በዲላ 5.8፣ በጭራ 5.3፣ 22.7፣ ፣ በአዋሳ 4.5፣ በእምድብር 3.1፣ በጋቲራ 2.1፣ 10.5፣ 23.3፣ 16.5፣ በአማን 1.3፣ በቴፒ 1.2 ሚሜ፣ በአይደር 39.1፣ በአልጌ 20 እና12፣ በአርጆ 22.4፣ 22.6፣ በአፅቢ 46.2፣ በበደሌ 14.5፣ በቡሬ 13.6፣ 2.2፣ በደብረ ብርሃን 20.7፣ በደምቢ ዶሎ 26፣ በዳንግላ 20.8፣ 7.3፣ በጊምቢ 15.4፣ በካቺሴ 22.6፣ በላሊበላ 12.6፣ በላሬ 11፣ በማሻ 12.4፣ በንፋስ መወጪያ 11.7፣ በሻምቡ 10.8፣ ወግል ጤና 12.4፣ በወረኢሉ 15.7፣  ባበቱ 11.1 እንዲሁም በደብረማርቆስ 13፣ ሚሜ ይገኙበታል (ካርታ 1)፡፡ ከ4-10 የሚደርስ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 2)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35.0-43.0 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4) ።




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የፌብርዋሪ ወር በተለይም የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ የተስተዋለ ነበር፡፡ ይህም የነበረው ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ከነበረው የእርጥበት እጥረት ጋር ተዳምሮ በልግ ተጠቃሚ በሆኑት አካባቢዎች ላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረዉ፡፡ ነገር ግን በሁለተኛው አስር ቀናት እና በሶስተኛዉ ስምንት ቀናቶች በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምዕራብ የአገሪቱ ጥቂት ቦታዎች ላይ የአፈር ዉስጥ እርጥበት በመጠኑ እንደተሻሻለ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት በተለይም የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበረ፡፡ (ካርታ 5)፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 28/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የፌብርዋሪ ወር የነበረው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው ላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው ምስራቃዊ እና መካከለኛው ኪስ ተፋሰስ፣ በአባይ፣ በጥቂት ተከዜ፣ በአፋር ደናክል አዋሳኛ ተፋስስ እና በመካከለኛው ምዕራባዊ ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህ ለውሃማ አካላት ማሻሻል መጠነኛ አስተዋፅዎ ነበረው (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች ወር የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መደበኛ ቦታዎቻቸውን እየያዙና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ወር ነው፡፡ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሚፈጠሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ ይኖራል፡፡ በማርች የሚኖረው የዝናቡ መጠን ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ እስከ 30% የሚያገኙ ሲሆን፤ የመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ ከ20%-40% የሚሆነዉን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥለው የማርች ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብ  በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን  ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ፡፡

### 2.2 እ.አ.አ ከማርች 1-31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የማርች ወር በአንዳንድ የሀገሪቱ በልግ አብቃይ በሆኑ ስፍራዎች ላይ የሚጠበቀው መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበት የሚያሻሻል ሲሆን ይህም ሁኔታ ከማርች ጀምሮ ለሚዘሩ ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎችን ለመዝራት፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት እንዲሁም የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ስለሚኖረዉ አርሶ አደሮች አርብቶ አደሮችና እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት አዎንታዊ ጎኖችን በላቀ ሁኔታ ለመጠቅም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት በማድረግ አሰፈላጊ የዘር ግብዓት ከወዲሁ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ከበልግ ውቅት ተለዋዋጭ ባህሪ ጋር ተያይዞ ሊኖር የሚችለውን ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የአፈርና የውሃ እቀባ ስራዎችን ለማከናወን በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ከወሩ አጋማሽ በኋላ በአንጻራዊ መልኩ ደረቃማ ቀናቶች ስለሚኖሩ በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ዉሃ በማሰባሰብ፣ ማቆርና በማከማቸት በደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ያስፈልጋል።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከማርች 1-31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውኃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በሚቀጥለው የማርች ወር በተወሰኑ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ማለትም የላይኛው እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ ባሮአኮቦ፣ አዋሽ እና በላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን እንዲሁም የላይኛው እና የመካከለኛው አባይ፣ የላይኛው ተከዜ እንዲሁም አፋር ደናክል መጠነኛ እርጥበት እንደሚገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተወሰነ ደረጃ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት እንዲሻሻል የሚያድርግ ቢሆንም በዚህ ወቅት የቀኑ ሙቅት መጨመር ጋር ተያይዞ በውሃ አካላት ላይ ከፍተኛ የትነት መጠን የሚኖርበት ወቅት በመሆኑ የውሃ ሀብት በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et